ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

# የክቡር ዶ/ር ሀይሌ ወ/ሚካኤል አጭር የሕይወት ታሪክ

## ክቡር ዶ/ር ሀይሌ ወልደሚካኤል፣

- ግንቦት 21 ቀን 1925 ዓ.ም ጉምሻ በሚባል መንደር፣በአሁኑ አከላለል በጉራጌ ዞን ዱንቁላ (እንደገኝ) ወረዳ ከአባታቸው ከአቶ ወ/ሚካኤል ሆቅበቶ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ መከሬ ሀፌ ተወለዱ::
- የልጅነት ሕይወታቸው በባላገሩ ደንብ በከብት እረኝነት ተጀምሮ በ1934 ዓ.ም ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በትውልድ አካባቢያቸው በነበረው ሁኔታ በአካባቢው ቄስ መምህርት ትምህርት ጀመሩ:: ይህንኑ የቄስ ትምህርት አዲስ አበባ ድረስ ዘልቀው ቀጥለው፣በወላጅ አባታቸው ድንገተኛ ሞት ምክንያት ካቋረጡ በኋላ በ1942 ዓ.ም ዘመናዊ ትምህርት በደዛችማች ወንዲራድ ትምህርት ቤትና ኮከበ ፅባህ ት/ቤቶች ቀጥለዋል:: ከዚያም ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ወደ ሆነው ሆሳህና ከተማ በመመለስ በራስ አባተ ቧያለው ት/ቤት በመግባት በ1944 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በማለፍ ሐረር መምህራን ማሰልጠኛ ት/ቤት በ1945 ዓ.ም ገብተው ተምረዋል:: ከዚያ የነበረው የኑሮ ሁኔታ ስላልተመቻቸላቸው በ1946 ዓ.ም አቋርጠው ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ካሳንችስ በነበረው የመርሀ ዕውራን ት/ቤት በመምህርነት ተቀጥረው ሠርተዋል:: በዚሁ ወቅት በማታና በተልዕኮ ትምህርታቸውን ቀጥለው በ1950 ዓ.ም የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በማለፍ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ገብተው በ1953 ዓ.ም በታሪክ ትምህርት በዲግሪ ተመርቀዋል:: ከዚያም በ1954 ዓ.ም በደብረብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ት/ቤት በመምህርነት ከዚያም ዳይሬክተር ሆነው አገልግለዋል::
- በ1955 ዓ.ም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካን ሀገር በመሄድ በዩኒቨርስቲ ኦፍ ዩታህ በትምህርት አስተዳደር መስክ የማስተሬት ዲግሪያቸውን በ1958 ዓ.ም ካገኙ በኋላ ለዶክተሬት የሚያበቃ ትምህርት አገባደው ወደ ሀገር ተመልሰዋል::
- በ1958 ዓ.ም የዩታህ ተማሪ ከነበረችዋ የጉዋም (USA) ዜጋ ትሪንዳድ ጋር ተጋብተው አራት ልጆች (2ሴቶች እና 2 ወንዶች) ወልደው በሀገር ውስጥና በውጭ አስተምረዋል:: እንደዚሁም የታናሽ እህታቸውን ልጆች፣ታናሽ እህታቸውንና ሌሎችም የዘመድ አዝማድ ልጆች አስተምረው ለከፍተኛ ደረጃ አብቅተዋል፣ ሕይወታቸው እስከምታልፍ ድረስም 5 የሙት ዘመድ ልጆች ሰብስበው በማሳደግና በማስተማር ላይ ነበሩ::
- ጥቅምት 16 ቀን 1958 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የልዑል ባዕደማርያም የመሰናዶ ት/ቤት ዳይሬክተር ሆነው በመመደብ ሠርተዋል::
- በ1960 ዓ.ም ወደ አ.አ ዩኒቨርስቲ የትምህርት ፋክሊቲ በመምህርነት ተመድበው እየሠሩ በተጓዳኝ ለፒ.ኤች.ዲ. የሚያበቃቸውን የምርምር ሥራ በማካሄድ አጠናቀው በ1965 ዓ.ም የፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪያቸውን ከዩኒቨርስቲ ኦፍ ዩታህ አግኝተዋል::
- በ1962 ዓ.ም «የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ም/ፕሬዚዳንት»፣ ከዚያም በ1964 ዓ.ም ፕሪዚዳንት ሆነው በመመረጥ ለሀገራችን የትምህርት ስርዓት መጐልበትና ለመምህራን መብት መከበር፣ ይደረግ በነበረው ትግል፣ በሀገሪቱ ፖለቲካ ሕይወት ውስጥ እጅግ ፈታኝ በሆነ ወቅት አመራር ሰጥተዋል::
- በ1966 ዓ.ም በታወጀው የዕድገት በሕብረት ዘመቻ ዋና ጽ/ቤት የፕሮግራሞች አስተባባሪ ሆነው በመመደብ እጅግ ፈታኝ የሆነውን ሃላፊነት ተወጥተዋል::

- በ1969 ዓ.ም «የባህል ሚኒስቴር» ሆነው በመሾም እስከ 1971 ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ በጣም አስቸጋሪ በሆነ ወቅት መሥሪያ ቤቱን መርተዋል፡፡ ከዚያም መደበኛው ሙያቸው ወደሆነው የዩኒቨርስቲ መምህርነት ሥራቸው ተመልሰው በአ.አ. ዩኒቨርስቲ በረዳት ፕሮፌሰርነት አገልግለዋል፡፡ በምርምርና ስነ-ፅሑፍ ረገድም ከ40 ባላይ ጥናታዊ ፅሑፎችን ያሳተሙ ሲሆን «አብሮነት በኢትዮጵያ» በሚል መጽሐፋቸው ስለ ኢትዮጵያ የአካባቢው ሕዝቦች አንድነት ያላቸውን ራዕይ ይፋ በማድረግ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ሥራ ማበርከታቸው ተጠቃሽ ነው፡፡
- በ1975 ዓ.ም በብሔረሰቦች ጉዳይ ኢንስቲትውት የማህበራዊ ዘርፍ ሃላፊ በመሆን ተመድበው የኢሕዴሪ የሕገ-መንግሥት ቀረፃ ተልዕኮ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክተዋል፡፡
- በዚህ ሕገ-መንግሥት መሠረት በ1980 ዓም ላይ በተቋቋመው «የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ (ኢሕዴሪ) መንግሥት ውስጥ በመንግሥት ምክር ቤት በሚኒስትር ማዕረግ የአስተዳደር ዘርፍ ሃላፊ በመሆን የኢሕዴሪ መንግሥት ማብቂያ እስከ ሆነው 1983 ዓ.ም ድረስ አገልግለዋል፡፡
- ከዚያም ኢሕአዴግ የመንግሥት ስልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ በጠራው የሰላምና ዴሞክራሲ ኮንፌንስ ላይ የጉራጌ ማህበረሰብ ለመሳተፍ በወሰነው መሠረት «የጉራጌ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር» (ጉሕዴግ) ተመስርቶ ከድርጅቱ ሁለት ተወካዮች አንዱ በመሆን የጉባዔው ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከዚያም ከኮንፍረንሱ በኋላ የተቋቋመው የሽግግር መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል በመሆን አገልግለዋል፡፡
- በ1984 ዓ.ም በሽግግሩ ተወካዮች ም/ቤት በነበሩት 6 የደቡብ የብሔር ብሔረሰቦች ድርጅቶች እና ከም/ቤት ውጭ የነበሩት ሌሎች አራት ድርጅቶች ጥምረት የሆነውን «የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት» በማቋቋም ሂደት ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል፡፡
- የሽግግሩ ወቅት አብቅቶ በ1987 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫም በሽግግሩ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባል ከነበሩት ድርጅቶች አባላት ጋር በመሆን በመሠረቱትና «የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ» ይባል በነበረው አማካይነት በትውልድ አካባቢያቸው በእንደጋኝ የምርጫ ክልል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወዳድረዋል፡፡
- የረዥሙን አመታት የመምህርነት፣ የመንግሥት ባለሥልጣንነትና የፖለቲካ ተሳትፎ አብቅተው በጡረተኛ ነት የግል ኑሮ ከጀመሩ በኋላም ማህበራዊ እንቅስቃሴአቸው አልተገታም ነበር፡፡ በዚህ ረገድ «የአፍሪካ ቢዚነስ ኢንተር ናሽናል» የሚል ኩባንያ አቋቁመው አርአያነት ያለው ዘመናዊ የንግድ እንቅስቃሴ ማካሄድ መክረዋል፡፡
- ዶ/ር ሀይሌ ማህበራዊ ተሳትፎአቸው እጅግ ከፍተኛ የሆነ ምርጥ ዜጋ ናቸው፤ ለአብነት ያህልም የሚከተሉት ውሏቸው ተጠቃሽ ናቸው:-
    - በገጠር ልማት ለመሳተፍ በነበራቸው ፅኑ ፍላጐት ተነሳስተው በጉራጌ

መንገዶች ሥራ ድርጅት ውስጥ የቀድሞውን መራብቾና ቡሻና ምክትል ወረዳን በመወከል ከ1960 አጋማሽ ጀምሮ አስተዋጽዖ አድርገዋል፡፡ እንዲሁም «የጉራጌ ሕዝብ ራስ አገዝ ልማት ድርጅት» የሥራ አመራር ቦርድ አባል በመሆን ሰፊ አስተዋፅዖ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

- በትውልድ አካባቢያቸውና በመላው ኢትዮጵያ ትምህርት እንዲስፋፋ በነበራቸው ፅኑ እምነት ተነሳስተው የትምህርት ዕድል አግኝተው አዲስ አባባ የሚኖሩትን የአካባቢውን ተወላጆች (የሀዲያ፣የጉራጌ-እንደጋኝ፣ የከምባታ፣የስልጤ ወዘተ) በማስተባበር «የተምሮ ማስተማር ማህበር» በማቋቋም ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ መርተዋል፤ መደበኛ ት/ቤቶች እንዲከፈቱም ከፍተኛ ጥረቶች አድርገው በእጅጉ የተሳካላቸው የሀገሪቱ ምርጥ ልጅ ነበሩ ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

- የኢትዮጵያ የኩላሊት ህመም ማህበር መሥራችና ከ1987 እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ ምክትል ሊ/መንበር፣ ከዚያም የቦርድ አባል በመሆን ለማህበሩ መጠናከር ሳይታክቱ ሠርተዋል፡፡
- ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ የአፍሪካ ቤዛ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በፕሬዝዳንትነት በመምራት በኢትዮጵያና በአፍሪካ ውስጥ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ይረዳሉ ያሏቸው ዓላማዎች ዕውን እንዲሆን ሳይታክቱ ሲሰሩ ነበር፡፡
- በተለያዩ የአፍሪካ ክፍሎች በዘርና በሃይማኖት የተመሠረቱ የግጭቶች ባህል ካልተገታ በስተቀር ኢትዮጵያን ጨምሮ አፍሪካን ከባድ ችግር ውስጥ እንደሚካተት በነበራቸው ስጋት ተነሳስተው « የአፍሪካ የሰላምና የግጭት ማናጅመንት ጥናት ማዕከል» የተሰኘ ድርጅት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ምሁራን ጋር በመሆን አቋቁመው እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ነበር፣
- በሀገራችን በ1997 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ መንስዔነት የተፈጠረው አሳዛኝ ሁኔታ ያስተካከለውን ቀውስ በዕርቀ ሰላም ለማርገብ የተቋቋመው የሰላም ኮሚቴ ንቁ አባል በመሆን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሲያደርጉ የነበሩ ታላቅ የሰላምና የፍቅር ሰው ነበሩ፡፡

እኚህ ታላቅ የኢትዮጵያ ብርቅዬ ልጅ፣ አንድ የደሃ ገበሬ ልጅ ጥቅጥቅ ካለው ኋላ ቀር የባላገር ኑሮ ተነስቶ በቆራጥነት በሚያደርገው ጥረት ማንም ቅምጥሉ የጌታ ልጅ እን ን መድረስ የማይችልባቸው የዕውቀትና

የሃላፊነት ደረጃዎች መድረስ እንደሚቻለው የሚያሳይ ታሪክ ሠርተው ያለፉ የኑሮ ስኬት ተምሳሌት ናቸው፡፡

- ዶ/ር ሀይሌ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎቻቸው እንደ አባትና ታላቅ ወንድም የሚወደዱና የሚፈቀሩ፣ ሁሉንም ዜጋ በዕኩል አይን የማየት ፀጋን የተላበሱ፣ ከቅርብ ቤተሰባቸው አልፈው እርዳታ የሚሹና፣ የተቸገሩ ዜጐችን በሙሉ በትምህረት ዕድሜ ላይ ያለውን በማስተማር፣ ሥራ አጡን ሠርቶ የሚኖርበትን መላ በማፈላለግ፣ ለራሳቸው ሳይሆን ለሰው የኖሩ ሰብአዊነትን የተላበሱ መተኪያ የማይገኝላቸው ታላቅ ዜጋ ነበሩ!
- እነሆ ታላቁ ሀገር ወዳድ የሰላምና የፍቅር ሰው ብዙ ያቀዷቸውን ሀገራዊና ማህበራዊ ዕቅዶቻቸውን ሳያጠናቅቁ በተወለዱ በ76 ዓመታቸው ሳይታማሙ፣ ሳይጨነቁ፣ታጥበው ተዘጋጅተው፣ የቤተሰብ ጉባዔም ጠርተው ባለበት ሁኔታ የሰላም ዕንቅልፍ በድንገት አሸለቡ! *የሰላም ሰው ናቸው ያለጭንቅና ጠአር ከዚህች ዓለም ሰላማዊ ስንብት አድርገዋል!*

ቸሩ ፈጣሪያችን ለልጆቻቸው፣ ለእህቶቻቸው፣ ላሳደጓቸውና ለማሳደግ ላሰባሰቧቸው ወጣት የሙት ልጆች፤ ለመላውም ወዳጅ ዘመዶቻቸው ሁሉ መፅናቱን እንዲሰጥ እንለምናለን!